የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

የጋራ ልማት አፈፃፀም መመሪያ

517/2013

--------- 1996 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

1. መግቢያ

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ኤክስፖርት መር በሆነው የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ውስጥ ብቁ ተወዳዳሪ ሆነው ስልማቱ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ይጠበቃል:: እንዲያውም አሁን ባለው የአገሪቱ ኢንዱስትሪ ደረጃ ስትራቴጂውን ለማስፈጸም እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ የልማት ድርጅቶች ከሚያንቀሳቅሱት ሀብትና ካላቸው አቅም አንፃር የመሪነት ሚና መጫወት አለባቸው:: በተጨማሪም በልማት ስትራቴጅው የተቀመጠውን ዓላማ ለማሣካት ከግል ባለሀብት ጋር አብሮ መሥራት ይኖርባቸዋል::

የልማት ድርጅቶች ብቁ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ቢፈለግም አብዛኞቹ ከማኔጅመንትደ ከአሠራር፣ ከቴክኖሎጂ እና ከካፒታል በተያያዙ ችግሮች ምክንያት ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ አዳግቷቸዋል:: እነዚህን ድርጅቶች ወደ ግል ባለቤትነት በአያዋ በአጭር ጊዜ ለማዞር የተደረገው እንቅስቃሴም በተጠበቀው ፍጥነት ሊከናወን አልቻለም::

ስለሆነም የልማት ስትራቴጂውን ለማሳካት እና የልማት ድርጅቶችን የብቃት ችግር በወቅቱ ለመቅረፍ አቅም ካለው የግል ባለሃብት ጋር በጋራ ልማት ትብብር በቅንጅት በመሥራት በኤክስፖርት የተቀኙ ተወዳዳሪ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን በአጭር ጊዜ ማፍራት ይቻላል ተብሎ ይታመናል:: በሌላ በኩል ገቢ ምርቶችን የመተካት ሚና ያላቸው ድርጅቶችም ቢሆኑ ከአጋር ጋር በመሥራት ተወዳዳሪነታቸውንና የገበያ አድማሣቸውን እንዲያሠፉ ማድረግ አግባብ ነው::

በመሆኑም የጋራ ልማቱን (Joint Investment) ሥርዓት ባለው መንገድ ለመምራት መመሪያ ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ሆኗል:: ይህ መመሪያ በጋራ ልማት ከኮንትራት በፊት ቅድመ ዝግጅቶችንደ በኮንትራክት ወቅት የሚታዩ ጉዳዮችንና ከኮንትራክት በኋላ ያሉ የአፈፃፀምና የክትትል ሥራዎችን ያካተተ ነው::

የጋራ ልማት ማስፈፀሚያ መመሪያ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 277/94 መሠረት ሕጋዊ ሰውነት አግኝቶ ሲቋቋም በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በኢንቨስትመንት አዋጅ 280/94 አንቀፅ 7 ከተሰጠው ሥልጣን መንጭቶ የተዘጋጀ ነው::

2. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ መመሪያ ውስጥ:-

2.1 " የጋራ ልማት " ማለት በአዋጅ 25/84 ወይም በአዋጅ 146/94 የተቋቋመ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ ወይም መንግሥት የአክሲዮን ድርሻ ባለቤትነት ያለበት ድርጅት ወይም ወደተግባር እንዲሸጋገር የተወሰነን የመንግሥት የልማት ፕሮጀክት በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ሲወከል በመንግሥትና በግል ወይም የውጪ መንግሥታዊ ተባባሪ ድርጅት መካከል የሚደረግ የልማት ስምምነት ወይም ኮንትራት ሲሆን በኮንትራቱ መሠረት

በሚቋቋመው የአክሲዮን ማኅበር ውስጥ ተባባሪው የተወሠነ አክሲዮን (Share) ባለቤት የሚሆንበት ነው ::

2.2 " ተባባሪ " ማለት በመንግሥታዊ የልማት ሥራ ለመሣተፍ የሚፈልግ የልማት ተባባሪ ነው::

2.3 " ሚኒስቴር " ማለት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው::

2.4 " ባለሥልጣን " ማለት በአዋጅ 277/94 የተቋቋመ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ነው::

2.5 " ድርጅት " ማለት በምርት እና/ወይም በአገልግሎት ሥራ ላይ የተሠማራ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ሥር የሚተዳደርና ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል መንግሥታዊ የሆነ የልማት ድርጅት ነው::

2.6 " ቦርድ " ማለት በባለሥልጣኑ የሚሠየምና መንግሥትን ወክሎ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን የሥራ እንቅስቃሴ የሚከታተል ወይም በንግድ ሕግ የተቋቋመ የአክሲዮን ማኅበር የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም በባለሥልጣኑና በውጭ ተባባሪው ወገን በጋራ የሚሠየም የሥራ አመራር ቦርድ ወይም የዲሬክተሮች ቦርድ ነው::

2.7 "የመግባቢያ ሠነድ " ማለት መንግሥታዊ የልማት ድርጅትና አጋር የሚሆነው ተባባሪ ወደ ሙሉ ስምምነትና ኮንትራት ከመግባታቸው በፊት የሚፈራረሙበት የመግባቢያ ሠነድ ነው::

2.8 "የጋራ ልማት ኮንትራት " ማለት መብትና ጥቅሞችን እንዲሁም ግዴታዎችን በተመለከተ በተባባሪ ወገኖች መካከል የተደረገ የመጨረሻ ስምምነት ወይም የውል ሠነድ ነው ::

2.9 "የማኅበር መመሥረቻ ደንብ እና የማኅበር መተዳደሪያ ደንብ" ማለት በንግድ ሕጉ እንደተጠቀሰው በዓላማዎች፣ በአደረጃጀት መርሆዎችና በማኔጅመንት ዘዴዎች ዙሪያ፣ ወዘተ በተባባሪ ወገኖች መካከል የጋራ ልማት ውሉን መሠረት አድርጎ የተዘጋጀ የባለአክሲዮኖች የስምምነት ሰነድ ነው::

3. ዓላማዎች

መመሪያው የሚከተሉትን ዓለማዎች የሚያሣካ ነው::

3.1 አጋሮችን በተለያዩ አማራጮች በማግኘትና በጋራ ልማት በማስገባት የልማት ድርጅቶችን የመወዳደር አቅም በካፒታልዶ በማኔጅመንትና በቴክኖሎጂና በገበያ አመራር ማጠናከር/መገንባት፤

3.2 የአጋር ፍለጋ፣ አቀባበል፣ የፕሮፖዛል ግምገማና ውሣኔዎችን የማስተሳሰሩ ሂደት ወጥ በሆነና በሚታወቅ አሠራር እንዲመራ ማድረግ፤

3.3 አጋር የመፈለጉና የማስገባቱ ሂደትና አሠራር ስለስሥልጣኑ በሕግ በተሰጡ ኃላፊነቶችና ተግባራት መሠረት መሆኑን ማረጋገጥ፤

3.4 ስትራቴጂክ ጠቀሜታ ኖሯቸው መንግሥት ከግል ባለሀብት ጋር በጋራ ለማልማት ስሚያስባቸው ፕሮጀክቶች አጋር በማግኘትና በማስገባት ሥራዎች እንዲከናወኑ ማድረግ፤

3.5 የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ከአጋር ጋር በመሥራት ተወዳዳሪ ሆነው በውጪ ገበያ ትርጉም ባለው መንገድ እንዲሣተፉ ማድረግ እንደዚሁም ገቢ ምርቶችን በዋጋ ጥራት ተወዳዳሪ ሆነው እንዲተኩ ማብቃት፤

4. አጋር የማስገቢያ መንገዶች/ አማራጮች

በመሠረቱ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጪ አጋር የሚሣተፍበት ፖርትነርሺፕ ዓይነት የተለያየ ሊሆን ቢችልም አጋሩ ከሚገባበት የልማት ድርጅት በአንድ ወይም በሌላ መንገድ የሚሻልበት ብቃት ሊኖረው ይገባል:: ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ አጋሩ በሚከተሉት አማራጮች ሊሣተፍ ይችላል::

4.1 በኢኩቲ መዋጮ (Equity Contribution)

ሀ/ ይህ አጋሩ በዓይነት ወይም በገንዘብ የሚመዘን መዋጮ ይዞ እንደሚመጣ ያመለክታል:: የመዋጮው ዓይነት ገንዘብ፥ መሣሪያዎች የአዕምሮና የኢንዱስትሪ ንብረትና የቴክኖሎጂ ዕውቀት (Know-how) ወይም ሌላ ቋሚ ወይም ተንቀሣቃሽ ንብረት ሊሆን ይችላል::

ለ/ በማናቸውም መንገድ የሚዋጣው ሀብት አግባብ ባለው ሕጋዊ አሠራር ተተምኖ የገንዘብ ዋጋ ሊኖረው ይገባል::

ሐ/ በመዋጮ የሚመሠረተው የጋራ ኢንቨስትመንት ነባሩን የመንግሥት ልማት ድርጅት ሕጋዊ ሠውነት ሳይለውጥ ወይም ሙሉ በሙሉ ሊለውጥ ይችላል::

መ/ በተጨማሪም በኢኩቲ መዋጮ የሚመሠረተው የጋራ ልማት ከነባር ድርጅት ውጪ ተጠንቶ ባለ ፕሮጀክት ላይ የተመረኮዘ ሊሆን ይችላል::

ሠ/ አንድን ሥራ/ ፕሮጀክት በጋራ ለመሥራት በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች የኢኩቲ መዋጮ ለአጭር ጊዜም ቢሆን ሊፈፀም ይችላል::

4.2 በኢኩቲ ያልሆነ መዋጮ (Non- Equity Contribution)

ሀ/ ይህ በንግድ ምልክት /ብራንድ፣ በላይሰንስ፣ በወጪ ገበያ (access to foreign market) በንብረት ወይም በይዞታ ኪራይ (Premise renting) በቴክኒክ/ ቴክኖሎጂ ድጋፍ፣ ወዘተ ሊከናወን የሚችል ሆኖ

በልማት ድርጅቱ የባለቤትነት ይዞታ ላይ በሙሉም ሆነ በከፊል ለውጥ የሚያመጣ አይሆንም::

ለ/ የአንድን ልማት ድርጅት ቅጥር ግቢ /ፋሲሊቲ በመጠቀም በውስታ ላይ የተመሠረተ የባለቤትነት ለውጥ የማያመጣ አጋርነት ሲመሠረት ይችላል::

ሐ/ በፊደል "ሀ" በተቀመጠው መልክ የሚመሠረተው ፓርትነርሽፕ እንደሁኔታው ለአጭር ወይም ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ሲሆን ይችላል::

4.3 በሲኩቲ መዋጮ ሆነ ያለ ሲኩቲ መዋጮ የአጋርነት ጥያቄው መንግሥት ባለአክሲዮን ለሆነበት ድርጅት ከቀረበ ጉዳዩ በንግድ ሕጉ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል:: ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት የባለቤትነት መብት ማስከበር ያለበት የተቆጣጣሪው ባለሥልጣን በመንግሥት ጥቅም ላይ ተፅዕኖ የሚያሣድር ጉዳይ ሲያጋጥመው ጉዳዩን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ አቅርቦ ማስወሰን አለበት፡

5. አጋር የማፈላለግና የማስገባት ሂደቶች

አጋር በሚከተሉት አማራጮች ሊገኝ ይችላል::

5.1 በአጋሩ በራሱ ፍላጎትና ጥያቄ

5.1.1 የጥያቄው አቀራረብና ይዘት

አንድ አጋር የተሣትፎ ፍላጎቱን ለልማት ድርጅት፣ ለተቆጣጣሪው ባለሥልጣን፣ ለሚኒስቴሩ መ/ቤት ወይም ለሌላ አግባብ ላለው የመንግሥት አካል በመግለፅ የአጋርነት ጥያቄውን ሲያቀርብ ይችላል:: በማናቸውም ሁኔታ አጋሩ ቢመጣ ጥያቄው ለባለሥልጣኑ መ/ቤት በፅሁፍ ከአባሪ የፕሮጀክት ሀሣብ/ፕሮፖዛል ጋር መቅረብ ይኖርበታል:: አጋሩ የሚያቀርበው ፕሮፖዛል የሚከተሉትን የሚሸፍን ይሆናል::

ሀ/ ስለአጋሩ ማንነት፣ ዜግነት፣ ቋሚ አድራሻ፣ የሥራ ሥምሪት፣ ወዘተ፤

ለ/ ለአጋርነት የሚፈልገው የሥራ መስክ ወይም የልማት ድርጅት ወይም ፕሮጀክት፤

ሐ/ የአጋርነቱ ዓላማ፣ ይዘት፣ ቆይታ ጊዜ እና ከተግባራዊነቱ የሚጠበቅ ውጤት፤

መ/ ዝርዝር የቢዝነስ ፕላን ወይም የአዋጪነት ጥናትዶ ወይም የፕሮጀክት ሀሣብ፤

ሠ/ የሚሣተፍበት የአጋርነት ዓይነት ዐሲኩቲ ወይም ከሲኩቲ ውጪ) እና እንዲኖረው የሚፈልገው ድርሻና የመዋጮ መጠን፤

በሬደል "ሀ" እና "ለ" የተመለከቱትን ማንም የአጋርነት ጥያቄ የሚያቀርብ አካል በግልፅ ከመጀመሪያውኑ ማሣወቅ ያለበት ሲሆን በሬደል "ሐ" ፣ "መ" እና "ሠ" የተመለከቱት በሂደት ሊቀርቡ ይችላሉ:: ነገር ግን በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን የመጨረሻ የአጋርነት ውስታ ከመፈረሙ በፊት ሁሉም ተሟልተው ሊገኙ ይገባል::

5.1.2 ጥያቄው የሚስተናገድበት ሂደት

አንድ አጋር ከአንድ የልማት ድርጅት ወይም ፕሮጀክት ጋር በጋራ ለመሥራት ጥያቄ ለተቆጣጣሪው ባለሥልጣን፣ ለልማት ድርጅት/ ለሚኒስቴር መ/ቤት ወይም ለሌላ አግባብ ላለው የመንግሥት አካል ሊያቀርብ ይችላል:: ሆኖም ዝርዝር ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት የአጋርነት ጥያቄው በፅሁፍ ለተቆጣጣሪው ባለሥልጣን መቅረብ ይገባዋል::

5.1.2.1 ጥያቄው በቀጥታ ለልማት ድርጅቱ ከቀረበ በጥያቄውና በአጋርነቱ ዓይነት ላይ ማኔጅመንቱና ቦርዱ ተወያይቶ ከአስተያየት ጋር በቦርዱ በኩል ለተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ያቀርባል:: የተቆጣጣሪውም ባለሥልጣን የቀረበውን ጥያቄና አስተያየት አገናዝቦ ቀጣይ ተግባራትን ይወስናልደ ይህንንም ለሚመለከታቸው አካላት በፅሁፍ ያሣውቃል::

5.1.2.2 የአጋርነት ጥያቄው በቀጥታ ለተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ከቀረበ ባለሥልጣኑ ፕሮፖዛሉ በሚመለከተው ድርጅት ሥራ አመራርና ቦርድ እንዲታይና ተገምግሞ ከአስተያየት ጋር በጊዜ ገደብ እንዲቀርብ ለድርጅቱ ቦርድ በፅሁፍ ያስተላልፋል:: የተሠጠውን ምላሽ በመያዝ በጉዳዩ ላይ ዝርዝር ውይይት ከድርጅቱ ቦርድና ማኔጅመንት ጋር በማድረግ በቀጣይ ሥራዎችና ሂደቶች ላይ ባለሥልጣኑ አቋም ይወስዳል፤

5.1.2.3 አጋሩ ላቀረበው ፕሮፖዛል ምላሽና አስተያየት ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከተቆጣጣሪው ባለሥልጣን በፅሁፍ ይሰጠዋል:: ይህ ጊዜ በቅድሚያ ከአጋሩ ሊቀርቡ የሚገባቸውን ተጨማሪ ማብራሪያዎች /ወይም ማስተካከያዎች እንዲቀርቡ የተደረገበትን ጊዜ ያካትታል:: ሆኖም ለተየጠቁ ማብራሪያዎች/ ማስተካከያዎች አጋሩ በወቅቱ ምላሽ ካልሰጠ ወይም በቂ መረጃ ካላቀረበ የሁለት ወሩ የጊዜ ገደብ ሊራዘም ይችላል::

5.1.2.4 አጋሩ ያቀረበው ፕሮፖዛል ተቀባይነት የሌለው ከሆነ ውጤቱ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በተቆጣጣሪው ባለሥልጣን በኩል ከነምክንያቱ በፅሁፍ ይገለፅለታል:: አጋሩ በተሰጠው ምላሽ ያልረካ ከሆነ ቅሬታውን ለባለሥልጣኑ ወይም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያቀርብ ይችላል::

5.1.2.5 ለልማት ድርጅቱና ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ሠፊ ጥቅም የሚያስገኝ ሌላ አጋር በተመሣሣይ ጊዜ ካልቀረበ ወይም አስገዳጅ ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር መጀመሪያ የመጣ አጋር በመጀመሪያ ይስተናገዳል::

5.2 <u>በመንግሥት ወይም በልማት ድርጅት ፍላጎት</u>

አጋር የመፈለጉና የማስገባቱ ሥራ በመንግሥት ወይም በልማት ድርጅት ተነሣሽነት (initiative) የሚከናወን ከሆነ የሚከተሉት አማራጮች አንድ ላይ ወይም በነጠላ እንዲገባቡ ሊወሰዱ ይችላሉ::

5.2.1 <u>በጨረታ/ በማስታወቂያ/ በቀጥታ መጥራት</u>

5.2.1.1 ከአንድ የበለጠ አጋር ለአንድ ድርጅት ወይም ፕሮጀክት ሊገኝ ይችላል ተብሎ ሲታመን የአጋር ፍለጋ በግልፅ በጫረታ ወይም ማስታወቢያ ጥሪ ሊካሄድ ይችላል::

5.2.1.1 ከሚታወቁ ውስን አጋሮች መካከል የተሻለውን አወዳደር ለመምረጥ የአጋር ፍለጋው በማስታወቂያ (short list) ጥሪ (invitation) ሊደረግ ይችላል፡

ከላይ በፊደል "5.2.1.1" እና "5.2.1.2" በተቀመጡ አማራጮች አጋር ሲፈለግ በልማት ድርጅቱ ወይም በባለሥልጣኑ የሚከተሉት በቅድሚያ የተዘጋጁ መሆን አለባቸው፤:

ሀ/ አጋሩ የሚሠማራበት ሀገራዊ ኢንዱስትሪ ባህሪ በአጭሩ፤:

ለ/ አጋር የሚፈለግለት ፕሮጀክት/ ድርጅት ፕሮፋይል ወይም አጭር መግለጫ፤

ሐ/ አጋር የሚፈለግበት የሥራ መስክና አጋሩ የተፈለገበት ዓላማ፤

መ/ ከአጋሩ የሚጠበቅ አስተዋፅ እና ውጤት፤

ሠ/ አጋሩ እንዲያሟላቸው የሚገቡ ቅድመ-ሁኔታዎች ኦ ካሉ)

ረ/ አጋር ለማግኘት/ ለማስገባት የተሻለ ነው የሚባለው አማራጭ ኦግልፅ ጫረታዶ ውስን ጫረታ ወይም ቀጥታ ጥሪ) እና አማራጩ ለምን እንደተመረጠ አጭር ማብራሪያ፤

ሰ/ የተጫራቾች መመሪያ (Instruction to bidders)፤

ሸ/ የጨረታ ማስታወቂያ

የጨረታ ማስታወቂያው የጨረታ ጥሪ መልዕክት፣ ጨረታው የሚቀይበትን ጊዜና የሚከፈትበትን ቀን፣ የተጨራቾችን ግዴታ፣ ተጫራቾች የሚያቅርቧቸውን የቴክኒክ እና ፋይናንሻል

ፕሮፖዛሎችና የፕሮፖዛሎችን አቀራረብ፣ ወዘተ በግልፅ የሚያስረዳ መሆን አለበት::

5.2.1.3 የአጋር ፍለጋ ጨረታ እንዳስፈላጊነቱ በልማት ድርጅቱ ወይም በተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ሊቀርቡ ይችላሉ::

5.2.1.4 በጨረታ ወይም በማስታወቂያ ጥሪ የተገኙ የአጋርነት ፕሮፖዛሎች በየደረጃው በድርጅቱ ማኔጅመንትና ቦርድዶ ባለሥልጣን እንደዚሁም እንዳስፈላጊነቱ በገለልተኛ አማካሪ እንዲገመገሙ ተደርገው በፅሁፍ ለተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ውሣኔ ይቀርባሉ::

5.2.1.5 በቴክኖሎጂዶ በገበያ፣ በማኔጅመንት/ ወዘተ የተመሠከረለት ወይም የሚታወቅ ችሎታ / ብቃት ያለው አጋር አለ ተብሎ ሲታመን ወይም በሁለት ጨረታዎች በቂ ተወዳዳሪ ካልቀረበ የአጋር ፍለጋው በቀጥታ ጥሪ (Direct & tailored invitation) ወይም ከመንግሥት ጋር ሀገሪቱ ከገባችው ሥምምነቶች በሚመነጭ ሁኔታ ሊካሄድ ይችላል::

5.3 <u>የአጋርነት ምሥረታና ውጤት</u>

5.3.1 የሚመሠረተው አጋርነት አግባብ ያላቸውን የሀገሪቱን ሕጎች የሚያከብር የመሆን ግዴታ አለበት::

5.3.2 በማናቸውም መንገድ የሚገኝ የአጋርነት ጥያቄ ውጤት የሚኖረው በባለሥልጣኑ አቅራቢነት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ውሣኔ ተሰጥቶበት ሲፀድቅ ብቻ ነው:: የሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባለሥልጣኑ በቀረበለት የአጋርነት ውሣኔ ሃሣብ ላይ ከሁለት ሣምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ምላሽ በፅሁፍ መስጠት ይኖርበታል::

5.3.3 ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባለሥልጣኑ የሚቀርበው የውሣኔ ሀሣብ የፕሮጀክት ፕሮፖዛልዶ የቢዝነስ ፕላንና የጋራ ልማት ውለታ ያካተተ ይሆናል::

5.3.4 የአጋርነት ጥያቄው ተቀባይነት አግኝቶ ወደአፈፃፀም ሲገባ በነባር የልማት ድርጅት ሕጋዊ ሠውነት ላይ ለውጥ ሲያመጣ የሚችለው የአጋር ምሥረታው የልማት ድርጅቱን ህልውና አጥፍቶ ሌላ ድርጅት ወይም የአክሲዮን ማኅበር እንዲፈጠር የሚያደርግ ውጤት ሲኖረው ነው::

5.3.5 በንዑስ አንቀጽ 5.3.4 የተገለፀው ተፈፃሚ የሚሆን ከሆነ ነባሩን ድርጅት በሕግ የማፍረስና እንፓልፕል ሥራዎችን/ ጉዳዮችን የሚከታተል አካል እንዲሠየም የማስደረጉ ኃላፊነት የተቆጣጣሪው ባለሥልጣንና የሚኒስቴር መ/ቤቱ ይሆናል:: ይህ እንዳለ ሆኖ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ

የሚቀርበው የውሣኔ ኃሣብ በተቆጣጣሪው ባለሥልጣን በኩል የሚዘጋጅ ይሆናል።

5.3.6 አንድ የመንግሥት ልማት ድርጅት ካለው ንብረት የተወሰነውን ክፍል ብቻ በማዋጣት የአጋር ምሥረታው የሚካሄድ ከሆነ ሂደቱ የነባሩን ድርጅት ሕጋዊ ሰውነት አይቀይረውምደ ሆኖም በአጋርነቱ ምክንያት ሌላ ሦስተኛ ህጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት/ አክሲዮን ማኅበር ሊፈጥር ይችላል። በዚህ ጊዜ ነባሩ የልማት ድርጅት የራሱን መዋጮ ይዞ በአዲሱ ድርጅት/ አክሲዮን ማኅበር ውስጥ በህግ የተሰጠውን የባለቤትነት መብትና ግዴታውን እየተወጣ ይቀጥላል።

5.3.7 በአጋርነት ምሥረታ ወቅት ነባሩ ድርጅት ካለው ንብረት በተጨማሪ መዋጮ ማቅረቡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጥያቄው በድርጅቱ ቦርድ በኩል ለተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ቀርቦ ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ መዋጮ እንዲሆን በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊፈቀድ ይችላል።

5.4 የዋጋ ትመና (Valuation of Contribution)

5.4.1 አንድ የመንግሥት የልማት ድርጅት ለጋራ ልማቱ እንደመዋጮ ሆኖ ሲቀርብ የድርጅቱ ዋጋ (Value) በኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ወይም ኤጀንሲው በሚወክለው አካል ይዘጋጃል። በተወከለው አካል የተዘጋጀው ዋጋ በኤጀንሲው ፀድቆ ለተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ይተላለፋል።

5.4.2 በኤጀንሲው ወይም በወኪል የሚዘጋጀው ዋጋ የልማት ድርጅቱ የንብረት (asset) ወይም የኩባንያው ዋጋ (company value) ወይም ሁለቱንም ሊሆን ይችላል።

5.4.3 በንዑስ አንቀጽ 5.4.1 በተገለፀው መሠረት የተደረሰበት የልማት ድርጅቱ ዋጋ የመዋጮ መጠን መነሻ ሆኖ ይወሰዳል። ሆኖም በተለያዩ ምክንያቶች አጋሩ መነሻ መዋጮውን የማይቀበለው ከሆነና ከአጋሩ ጋር መሥራቱ የተሻለ ጥቅም በሂደት እንደሚያስገኝ ከታመነ ይኸው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ቀርቦ ሲወሰን የልማት ድርጅቱ ከመነሻ ዋጋ ያነሰ ዋጋ እንዳለው ተደርጎም የአጋር ምሥረታው ሲካሄድ ይችላል።

5.4.4 አጋሩ ለጋራ ልማቱ አያገለግሉም የሚላቸው ንብረቶች ተለይተው ለመንግሥት ቀሪ ከተደረጉ በኋላ በቀረው ዋጋ የአጋርነት ምሥረታው ሊካሄድ ይችላል።

5.4.5 ከአጋሩ ጋር በሚደረግ ድርድር የልማት ድርጅቱ በመነሻ ከተቀመጠው ዋጋ የበለጠም ተገምቶ ሥምምነት ሊደረስ ይችላል።

2.2. <u>የቋሚ ንብረቶች ዋጋ ትመና</u>

2.2.1 ትራክተሮችና ማምረቻ መሣሪያዎች የኢንዱስትሪና ኮንስትራክሽን መሣሪያዎች በሚተመኑበት ዘዴ በተመሳሳይ ይተመናሉ።

2.2.2 የእርሻ መሬት ለግል ባለሀብት በሽያጭ የሚዛወር ባለመሆኑ የመሬት ዋጋ በትመና ውስጥ አይካተትም። የሊዝ ዋጋውም በመሬቱ ባለቤት (ክልል መንግሥታት) የሚወሠን በመሆኑ በዋጋ ትመናው ውስጥ አይካተትም። ስለዚህ በትመናው የሚካተተው መሬቱን ለማልማት የወጣው ወጪ ሲሆን ይህም የሚከተሉትን ይይዛል።

- የተለያዩ የእርሻ መሬት ቅየሳ (Survey) ሥራዎች ወጪ፣
- የመሬት ንድፍ (ዲዛይን) ሥራ ወጪ፣
- የእርሻ መሬት ምንጣሮ ሥራ (Land Clearing) ወጪና፣
- የእርሻ መሬት ማስተካከል ሥራ (Land Leveling) ወጪና፣
- የእርሻ ውስጥ መንገድ ሥራ (Farm Roads) ወጪና፣
- የጐርፍ መከላከያ (Dyke) ሥራ ወጪና፣
- የአፈርና ውሃ እና የደን ጥበቃ ሥራ (soil, water & forest conservation works) ወጪ፣

2.2.3 የእርሻ መሬቱ በመስኖ የሚለማ ከሆነ ከላይ ከተጠቀሱት ወጪዎች በተጨማሪ የዋጋ ትመናው የሚከተሉት ይካተታሉ።

- የመስኖ ቦይ ቁፋሮ ሥራ ወጪ፣
- የመስኖ ድንጋይ ንጣፍ (Canal Lining) ወጪ፣
- ለመስኖ አገልግሎት የተቀበረ ቱቦ ወጪ፣
- ከላይ የተዘረዘሩትን ወጪዎች ታሳቢ በማድረግ በግብርና ዘርፍ የተሠማሩ ድርጅቶች የንብረት ዋጋ ትመና በሚከተለው ሁኔታ ይዘጋጃል።

2.2.4 በመሣሪያ (Heavy Duty Machine) የሚሠሩ የቁፋሮ፣ የምንጣሮና የማስተካከል፣ የልማት ሥራዎች ወጪዎች የሚከተሉትን መረጃዎች መሠረት ያደርጋሉ።

- የተመነጠረው/የተስተካከለው የእርሻ መሬት ስፋት መረጃ ይወሰዳል።

- አንድ ሄክታር መሬት በመሣሪያ ለመመንጠር/ለማስተካከል የሚያስፈልገውን የወቅቱ የኪራይ ዋጋ በመውሰድ በጠቅላላ የተመነጠረ/የተስተካከለ መሬት ስፋት ጋር በማባዛት የእርሻ መሬት ምንጣሮ/የማስተካከል ሥራ ዋጋ ይተመናል፡፡

2.2.5 በሰው ጉልበት የሚሠራ የቁፋሮ ሥራ ወጪ ግምት በሚከተለው መንገድ ይተመናል፡፡

- በአንድ የሰው ቀን (man-day) ሊቆፈር የሚችለው መጠን በሜትር ኩብ ይተመናል፡፡
- ጠቅላላው የቁፋሮ ሥራ በሜትር ኩብ ይሰላል፡፡
- ጠቅላላውን የቁፋሮ ሥራ ለአንድ የሰው ቀን በወቅቱ በሚከፈለው የጉልበት ዋጋ በማባዛት ለሥራው የሚያስፈልገው ወጪ ይተመናል፡፡
- በመስኖ ቦይ ላይ የተነጠፈ ድንጋይ ወይም ለመስኖ አገልግሎት የተዘረጋ ቱቦ ካለ በድንጋዩና በቱቦው የወቅቱ ዋጋ ላይ የማንጠፍና የመዘርጋት የጉልበት ወጪ ተጨምሮበት አጠቃላይ ወጪው ይሰላል፡፡
- የተለያዩ የቅየሳና የዲዛይን ሥራዎች ወጪ በወቅቱ ለአንድ ሄክታር በሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ መሠረት ይተመናል፡፡
- የአፈር፣ የውሃና የደን ጥበቃ ወጪ ከድርጅቱ በሚገኘው አማካኝ ዓመታዊ ወጪ መሠረት ይዘጋጃል፡፡

2.3. የቋሚ ተክል ዋጋ ትመና

የቋሚ ተክል የዋጋ ተመን የሚከተሉትን ነጥቦች ግምት ውስጥ በማስገባት ይሠራል፡፡

- የተክሉ ዓይነት፣
- የተክሉ ዕድሜ፣
- ተክሉ ያረፈበት የመሬት ስፋት (የተክሉ ብዛት)፣
- የተክሉ ምርታማነት፣
- የምርት መሸጫ ዋጋ፣
- የተተከለበት አካባቢ (Agro Ecology)፣
- የማልሚያ ወጪ፣

- የማምረቻ ወጪ፣

ከላይ የተጠቀሱትን መረጃዎች መሠረት በማድረግ የዋጋ ተመኑ በሚከተለው ቀመር ይሰላል፡፡

የቋሚ ተክሉ ዋጋ (Biological Asset Value) = የመመስረቻ ወጪ + (ዲስካውንትድ ጥቅም - ዲስካውንትድ ወጪ)

የመመስረቻ ወጪ በቀመሩ ውስጥ የሚካተተው ቋሚ ተክሉ የሚቀረው የወደፊት ዕድሜ ቢያንስ የመመስረቻ ጊዜን (Establishment Period) ያህል ከሆነ ብቻ ነው፡፡

2.4 በድርጅቱ /በእርሻ ልማቱ/ ቅጽር ግቢ ውስጥ የተተከሉ ቋሚ ተክሎች (ለምሳሌ እንደ ባህር ዛፍ ያሉ) ዋጋ ባሉበት ሁኔታ ተቆርጠው ቢሸጡ ሊያወጡ በሚችሉት የአካባቢው አማካይ የመሸጫ ዋጋ ይወሰዳል፡፡ እንደዚሁም በድርጅቱ /በእርሻ ልማቱ/ ውስጥ የሚገኙ እንስሳት (ከብቶች) በጥናቱ ወቅት ሊያወጡ በሚችሉት የአካባቢው አማካይ የገበያ ዋጋ ይወሰዳሉ፡፡

ክ ፍ ል አ ራ ት

3. የሆቴልና ንግድ ተቋማት የዋጋ ትመና

3.1. ቋሚ ንብረት

የሆቴልና ንግድ ተቋማት የቋሚ ንብረት የዋጋ ትመና የሚሠራው የተጠራቀመ የእርጅና ቅናሽን ከአዲስ የመተኪያ ዋጋ ላይ በማቀናነስ (DRC) ይሆናል፡፡

በሆቴልና ንግድ ተቋማት የሚገኙ ቋሚ ንብረቶች እንደሚከተለው ተከፋፍለው ሊታዩና መረጃ ሊሰባሰብባቸው ይችላል፡፡

- ለሆቴል አገልግሎት የሚውሉ ትላልቅ መሣሪያዎች (ለምሣሌ ጄኔሬተሮች፣ ቦይለሮች፣ ወዘተ)
- የቢሮ ዕቃዎችና መሣሪያዎች (Office Furniture and Equipment)
- የቡና ቤት፣ የምግብ ቤትና የመኝታ ቤት ዕቃዎች (Furniture and Fixture)
- የመብያና መጠጫ ዕቃዎች (Silver Ware and Glass Ware)

- የወጥ ቤት ዕቃዎች (Kitchen Utensils)
- የጨርቅ ውጤቶች (Soft Furnishings)
- ሌሎች (Others)

ከላይ የተጠቀሱት ንብረቶች በአብዛኛው ለሆቴል የሚያገለግሉ ሲሆኑ ለንግድ ተቋም በተመሣሣይ ዝርዝሩ ወይም ክፍፍሉ የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡

የንግድና የሆቴል ማሽነሪዎች በቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ (Straight Line Depreciation) የእርጅና ቅናሽ በማስላት DRC የሚሠራላቸው ሲሆን የሌሎች ንብረቶች ዋጋ የሚተመነው በሚከተለው መልክ ይሆናል፡፡

- የእያንዳንዱ ዕቃ አዲሱና ተመሳሳይ ዕቃ የወቅቱ የገበያ ዋጋ መረጃ ይሰበሰባል፡፡
- ከድርጅቱ ወይም ከሌላ አስተማማኝ ምንጭ በሚገኘው መረጃ መሠረት የኤጀንሲው ባለሙያዎች የድርጅቱ ቋሚ ንብረቶች ያሉበትን አካላዊ ይዞታ ከግምት በማስገባት በሚከተለው ሁኔታ ይሰላሉ፡፡

ተ.ቁ.	ደረጃ	ከመቶ የተሰጠው ነጥብ
1	በጣም ጥሩ	65-75%
2	ጥሩ	55-64%
3	መልካም	45-54%
4	ደካማ	25-44%

- ቋሚ ንብረቶቹ ላላቸው አካላዊ ይዞታ የተሰጣቸው መቶኛ በአዲስ ተመሣሣይ ዕቃ መተኪያ ዋጋ ይባዛና የእርጅና ቅናሹ ይቀነሣል፡፡
- የተበላሹና ሊወገዱ የሚገባቸው ወይም ከ25% በታች ደረጃ የተሰጣቸው ዕቃዎች የዋጋ ትመና ሳይዘጋጅላቸው ለገዥው ባለሃብት ይተላለፋሉ፡፡

3.2. ክምችት

ማንኛውም የሆቴልና የንግድ ተቋማት ክምችት በተገዛበት ዋጋ እና ወጪ የሚተመን ይሆናል፡፡ ሆኖም ለድርጅቱ አገልግሎት ሊውሉ የማይችሉ፣ በገበያ ላይ ተፈላጊነት የሌላቸው፣ የተበላሹ፣ ወዘተ ክምችቶች ተለይተው ከተመዘገቡ በኋላ በድርጅቱ በቅድሚያ ለሽያጭ እንዲወገዱ ይደረጋል፡፡ ከድርጅቱ ሽያጭ በፊት

የማይሸጡ ከሆነም የዋጋ ትመና ሳይዘጋጅላቸው ባሉበት ሁኔታ ለገዥ የሚተላለፉ ይሆናል፡፡

ክ ፍ ል አ ም ስ ት

4. የንግድ ዋጋ ትመና

4.1 የንግድ ዋጋ ትመና ዘዴ (DCF)

ሁለተኛው የድርጅት ዋጋ መተመኛ ዘዴ የንግድ ዋጋ ትመና ሲሆን የዚህ ትመና መሠረቱ የአንድ ድርጅት ዋጋ መመስረት ያለበት በንብረቶች ዋጋ ድምር ሳይሆን ንብረቶቹ በአጠቃላይ ለድርጅቱ ያስገኛሉ ተብሎ በሚታሰበው የወደፊት የተጣራ ገቢ /Earnings/ ይሆናል፡፡ በዚህም መሠረት የዋጋ ትመና ጥናቱ ሥራ የሚያተኩረው የወደፊት የድርጅቱን የማምረት አቅም፣ ሽያጭ፣ የወጪ መጠንና የድርጅቱ ዋና መሣሪያዎች ቀሪ ዕድሜ ላይ በሚደረጉ ትንተናዎች ላይ ተመስርቶ የዋጋ ትመናው እንደሚከተለው ይከናወናል፡፡

4.1.1 የድርጅቱ ቀሪ ኢኮኖሚያዊ ዕድሜ የሚወሰነው ድርጅቱ በትንበያ ዘመኑ ምንም አዲስ ኢንቨስትመንት ሳይደረግበት ሊቆይ የሚችልበትን ዘመን ዕድሜ በማስላት ነው፡፡ የአንድ ድርጅት የትንበያ ዕድሜ ተደርጎ የሚወሰደው አሥር ዓመት ሲሆን ይህ ግን እንደተጨባጭ ሁኔታው ማስተካከያ ሊደረግበት ይችላል፡፡

4.1.2 የድርጅቱ የማምረት አቅም የሚወሰነውም ምርቱ ተወዳድሮ ገበያ ማግኘት እስከቻለበት ያለው መጠን ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት የማምረት አቅሙ መጀመሪያ ዲዛይን የሆነበት ወይም ባለው ሁኔታ ሊደረስበት የሚችል ሆኖ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ሆኖም አንድ ድርጅት ባለፉት ሦስት ዓመታት ሙሉ አቅሙን ያልተጠቀመው በሥራ ማስኬጃ ወይም በግብዓት እጥረት ካልሆነ ሙሉ አቅሙ ለትመናው ሥራ ላይወሰድ ይችላል፡፡

4.1.3 ድርጅቱ ከሌሎች ሽያጮች የሚያገኘውን ገቢ በሚመለከት ያለፉት ሦስት ዓመታት አማካይ ገቢ እንዳለ ተወስዶ በትንበያ ዘመኑ ይካተታል፡፡

4.1.4 በቀጥታና በተዘዋዋሪ ለምርት የሚያገለግሉ ዕቃዎች ወጪ (Direct & Indirect Material Cost) ከምርት መጠን ጋር ታሳቢ ሆኖ የሚታይ ይሆናል፡፡

4.1.5 የሰው ጉልበት ወጪ በትመና ወቅት ባለው የድርጅቱ የሰው ኃይል መጠን እና የክፍያ ሁኔታ መሠረት ይወሰናል፡፡

4.1.6 የጥገና ወጪ እንደ ድርጅቱ ሁኔታ ባለፉት ሦስት ዓመታት የወጪ መረጃ መሠረት ሆኖ የጥገናው ወጪው ተመሳሳይ ወይም የመዋዠቅ ሁኔታ የሚታይበት ከሆነ ያለፉ ሦስት ዓመታት አማካይ ወጪ ይወሰዳል። ሆኖም የጥገና ወጪው እየጨመረ የመጣ ከሆነ በወጪው የእድገት ምጣኔ (Growth Rate) መሠረት ይሰላል።

4.1.7 የአስተዳደርና ጠቅላላ ወጪ (Administration & General Expense) የወጪው ዕድገት ምጣኔ በመቶኛ ተወስዶ ይሰላል።

4.1.8 የሽያጭ ወጪ (Selling and Distribution Cost) ከሽያጭ መጠን ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያለው ስለሆነ ያለፉት ሦስት ዓመታትን አማካይ በመመልከት ከሽያጭ እድገት ምጣኔ ጋር ተስተካክሎ ይሰላል።

4.1.9 የእርጅና ቅናሽ ስሌት የሚሠራው በድርጅቱ የአካውንቲንግ ፖሊሲ /Accounting policy/ የእርጅና ቅናሽ አሠራር ሆኖ፣ አዲስ በተተመነው ዋጋ ላይ ተመሥርቶ ይሆናል።

4.1.10 ድርጅቱ በሥራው ይቀጥላል ተብሎ ከተወሰደው ዕድሜ በፊት በእርጅና ምክንያት አገልግሎታቸውን የሚያቋርጡ ወሳኝ የማምረቻ መሣሪያዎች ካሉ የመሣሪያዎቹ የመተኪያ ዋጋ ተገምቶ ከአገልግሎት ውጭ ይሆናሉ በተባለው ዓመት ላይ በኢንቨስትመንት እንደሚተኩ ታሳቢ በማድረግ የካፒታል ወጪ ይያዛል።

4.1.11 ሌሎች ወጪዎች እንደሁኔታው በጥናቱ ወቅት በሚታዩ ሁኔታዎችና ከባለሙያዎች በሚቀርቡ ማብራሪያዎች መሠረት ይወሰናሉ።

4.1.12 ምንም እንኳን ስትመና ሥራ አንድ ድርጅት የተወሰነ ዕድሜ የተሰጠው ቢሆንም ድርጅቱ ከአሥር ዓመት በላይ እያመረተ/አገልግሎት እየሰጠ የሚቀጥል መሆኑ ከታመነበት በዕድሜው መጨረሻ ላይ በሚከተለው ሁኔታ የዋጋ ስሌት ተሠርቶ ተርሚናል ዋጋ እንዲካተት ይደረጋል።

$$ተርሚናል\ ዋጋ = \frac{\left[\dfrac{(በመጨረሻው\ ዘመን\ የሚኖረው\ ካሽ\ ፍሎ)*(1+የዕድገት\ ምጣኔ)}{(ማቀናነሻ\ ምጣኔ\ -\ የዕድገት\ ምጣኔ)}\right]}{(1 + የማቀናነሻ\ ምጣኔ)^n}$$

ከ፡- ማለት የድርጅቱ የገንዘብ ፍሰት ትንበያ የተሠራበት ወቅት (Cash Flow Period) ማለት ነው።

4.1.13 በገበ. ዘዴ /DCF/ በተገኘው ውጤት ላይ በድርጅቱ ይዞታ የሚገኙና ለተተነበየው የምርት መጠን አስተዋጽኦ ባያደርጉም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ቋሚ ንብረቶች (non-core assets) ዋጋ ባሉበት ሁኔታ ተተምኖ ይደመራል።

4.1.14 ለውሳኔ አሰጣጥ እንዲያመች በገበ. ዘዴ /DCF/ የሚዘጋጅ ትመና እንደ ኢንዱስትሪውና የድርጅቱ ተጨባጭ የገበያ ሁኔታና እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች የማቀናነሻ ምጣኔ አማራጭ የሚቀርብ ይሆናል።

4.1.15 የልማት ድርጅቶች (አ/ማህበራት) የዋጋ ትመና በሚሠራበት ጊዜ እንደልማት ድርጅቱ ባህርይ በትመና ወቅት ሲታዩ የሚገባቸው ሥጋቶች (Risk Factors) ሊለያዩ መቻላቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ግምት ውስጥ እንዲገቡ ይደረጋል።

- የአገሪቱ የገንዘብ ፖሊሲ ለውጥ
- የታክስ ፖሊሲ ለውጥ
- የገንዘብ ምንዛሪ ሁኔታ
- የድርጅቱ ምርት/አገልግሎት/ በገበያ ያለው ተፈላጊነት
- የአገሪቱ የዋጋ ግሽበት ሁኔታ
- የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ሁኔታ
- የአካባቢው ሁኔታ /የተፈጥሮ ሁኔታ/

4.1.16 በDCF የዋጋ ትመና ዘዴ በመጠቀም የዋጋ ትመና ለሚሠራላቸው የልማት ድርጅቶች ጥቅም ላይ የሚውለው የማቀናነሻ ምጣኔ (Discount Rate) ለምን እንደተመረጠ በጥናቱ ውስጥ በአግባቡ መገለጽ አለበት።

4.2 <u>በንግድ ዋጋ ትመና ጊዜ የተለየ ትኩረት የሚሹ ሴክተሮች</u>

4.2.1 <u>የእርሻ ልማቶች</u>

እያንዳንዱ ሴክተር የራሱ የሆነ ባህርይ ያለው በመሆኑ ይህንኑ ግምት ውስጥ ማስገባት ወሳኝ ነው። ከዚህ አኳያ የእርሻ ልማቶች የንግድ ዋጋ ትመና በሚዘጋጅበት ጊዜ ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ልዩ ትኩረት የሚሰጣቸው ይሆናሉ።

- የተክሉ ዑደት (Life-Cycle)

- የምርት መጠን እና ምርታማነት (ከአገር ውስጥና ከውጭ ጋር ሲነጻጸር)
- የአፈር ዓይነት፣ የአየር ፀባይ
- የአካባቢ ሁኔታ (Topography)
- የተክሉ ዕድሜ (Profile)
- የገበያ ሁኔታና ዋጋ
- የምርት ጥራት

4.2.2 የማዕድን ልማት ድርጅቶች

እንደ እርሻው ክፍለ-ኢኮኖሚ ሁሉ የማዕድናት ዘርፍም የተለየ ባህርይ ያለው በመሆኑ የዋጋ ትመና በሚሠራበት ጊዜ ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ልዩ ትኩረት የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡

- የማዕድኑ ክምችት (reserve) ሁኔታ፣
- ክምችቱ ጥቅም ላይ ቢውል የሚኖረው ዕድሜ፣
- የማዕድናቱ የጥራት ሁኔታ፣
- የማዕድን አወጣጡ ሁኔታ (open pit or deep/underground mining)፣
- ምርት (extraction rate)፣
- የገበያ ዋጋ ሁኔታ፣

የአንድ ድርጅት የንግድ ዋጋ ትመና ከመካሄዱ በፊት በቅድሚያ ማዕድናቱን በተመለከተ ዝርዝር ጥናት (detailed survey) በባለሙያዎች መካሄድ ይኖርበታል፡፡

ክ ፍ ል ስ ድ ስ ት

5. የልማት ድርጅቶች የመሸጫ ዋጋ አወሳሰን

5.1 አትራፊ ለሆኑ አክሲዮን ማህበራት

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አትራፊ ሆነው እስከተገኙ ድረስ የዋጋ ትመና የሚሠራው እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

- የንግድ ዋጋቸው ከተጣራ የንብረት ዋጋ በልጦ ከተገኘ የንግድ ዋጋው የጨረታ ጠቋሚ ዋጋ ይሆናል፣

- የንግድ ዋጋቸው ከተጣራ የንብረት ዋጋ (Net Asset) አንሶ ከተገኘ የተጣራው የንብረት ዋጋው የጨረታ መቋሚ ዋጋ ይሆናል።
- የተጣራው የንብረት ዋጋ ከዜሮ በታች ከሆነ ወይም የንግድ ዋጋው ከአክሲዮን ማህበሩ ዕዳ አንሶ ከተገኘ ድርጅቱ ወይም አክሲዮን ማኅበሩ ለጨረታ የሚቀርበው ያለ መቋሚ ዋጋ ይሆናል።

5.2 ከሳሪ ለሆኑ አክሲዮን ማህበራት

- የተጣራው የንብረት ዋጋ (Net Asset) ከዜሮ በላይ (Positive) ከሆነ የተጣራው የንብረት ዋጋ (Net Asset) የጨረታ መቋሚ ዋጋ ይሆናል።
- የተጣራው የንብረት ዋጋ (Net Asset) ከዜሮ በታች (Negative) ከሆነ አክሲዮን ማኅበሩ ያለ መቋሚ ዋጋ ለጨረታ ይቀርባል።

5.3 አትራፊ ለሆኑ የልማት ድርጅቶች

- አትራፊ ለሆኑ የልማት ድርጅቶች የንግድ ዋጋቸው ከንብረት ዋጋ በልጦ ከተገኘ የንግድ ዋጋው የጨረታ መቋሚ ዋጋ ይሆናል።
- የንግድ ዋጋቸው ከንብረት ዋጋ አንሶ ከተገኘ የንብረት ዋጋው የጨረታ መቋሚ ዋጋ ይሆናል።
- የድርጅቱ የንግድ ወይም የንብረት ዋጋ ትመና ከጠቅላላ ዕዳ በታች ሆኖ ሲገኝ የድርጅቱ የተጣራ ዕዳ የጨረታ መቋሚ ዋጋ ተደርጐ ይወሰዳል።

5.4 ከሳሪ ለሆኑ የልማት ድርጅቶች

- የንብረት ዋጋው ከጠቅላላ ዕዳው በልጦ ከተገኘ የንብረት ዋጋው የጨረታ መቋሚ ዋጋ ይሆናል።
- የንብረት ዋጋው ከጠቅላላ ዕዳው አንሶ ከተገኘ የድርጅቱ የተጣራ ዕዳ (Balance) የጨረታ መቋሚ ዋጋ ይሆናል።

ክ ፍ ል ሰ ባ ት

6. በርክክብ ወቅት ስለሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ አሰራርና ወሳሰን

6.1 ለአክሲዮን ማህበራት

አክሲዮን ማህበሩ ወደ ግል እንዲዛወር ሲደረግ በርክክብ ቆጠራ ወቅት ከትመናው በፊትም ሆነ በኋላ የአክሲዮን ማህበሩ ሀብት ባልሆነ ገንዘብ የተገዛ ወይም በስጦታ የተገኘ ንብረት ካለ ብቻ የርክክብ ልዩነት ዋጋ ትመና ይሠራለታል።

6.2 ለልማት ድርጅቶች

6.2.1 የጨረታ ጠቋሚ ዋጋው የንግድ ዋጋ ከሆነ በርክክብ ወቅት በመብለጥ Overage) የሚገኘው ንብረት ከትመናው ጊዜ በፊት የነበረ ንብረት ከሆነ የርክክብ ዋጋ ትመና አይሠራለትም። በመብለጥ የተገኘው ንብረት ከትመናው ቀን በኋላ የተገዛ ንብረት ወይም የተገነባ ህንፃ ከሆነ የርክክብ ልዩነት ዋጋ ትመና ይሠራል።

6.2.2 የጨረታ ጠቋሚ ዋጋ የንግድ ዋጋ ትመና ሆኖ በርክክብ ወቅት በማነስ (Shortage) የሚገኘው ንብረት ለንግዱ ቀጥተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርግ (Core Asset) ከሆነ የርክክብ ልዩነት ዋጋ ትመና ይሠራል። ከዚህ ውጪ በማነስ ለሚታይ ንብረት ግን የርክክብ ልዩነት ዋጋ ማስተካከያ አይሠራለትም።

6.2.3 የጨረታ ጠቋሚ ዋጋ የንብረት ዋጋ ትመና ከሆነ በመብለጥ (Overage) ወይም በማነስ (Shortage) ለተገኘው ንብረት የርክክብ ልዩነት ዋጋ ትመና የሚሠራው።

- በርክክብ ወቅት የተገኘው ቋሚ ንብረትና ክምችት በትመና ጊዜ ከታየው ንብረት የሚያንስ ከሆነ ቀደም ሲል በፀደቀው የዋጋ ተመን መሠረት ማስተካከያ ይደረጋል።
- በርክክብ ወቅት የተገኘው ቋሚ ንብረትና ክምችት በትመና ጊዜ ከታየው ንብረት የሚበልጥ ከሆነ በዚህ መመሪያ መሠረት ማስተካከያ ዋጋ ይሠራለታል።

6.2.4 ሰብሉ ርክክቡ በሚፈጸምበት ወቅት በደረሰበት የእድገት ደረጃ እንደገና ተገምቶ በጨረታ ሰነድ ላይ ካለው የሰብል ዋጋ ጋር በማገናዘብ ልዩነቱን ገዥው እንዲከፍል ይደረጋል። ነገር ግን ሠብሉ ሲመረት ይገኛል ተብሎ የተገመተው ገቢ

በትመናው ወቅት ተካትቶ ከነበረ ወይም ከሰብሉ የሚገኘው ምርት ወደ ገንዘብ ተለውጦ በዋጋ ትመና ጊዜ የተካተተ ከሆነ የርክክብ ልዩነት አይሠራለትም።

6.2.5 የእንስሳት/የከብቶች ርክክብ ልዩነት ዋጋን በተመለከተ በገጽ 13 በአንቀጽ 2.4 በተመለከተው መልክ ተፈጻሚ ይሆናል።

6.2.6 ክምችት ወይም በጉዞ ላይ ያለ ዕቃ ከሆነ በዚህ መመሪያ በገጽ 9 በአንቀጽ 1.2.2 እና 1.2.2 በተመለከተው የዋጋ ትመና ይሠራለታል። በጨረታ ሰነድ ላይ ከተመለከተው በልጦ ከተገኘ ገዥው ልዩነቱን ይከፍላል፤ አንሶ ከተገኘ ለገዥው ልዩነቱ ይቀነስለታል፣

6.3 በርክክብ ወቅት ስለሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ አወሳሰን

በቀድሞ መመሪያ እስከ 100,000 ብር ድረስ ያለውን የርክክብ ዋጋ ልዩነት በዋና ዳይሬክተር እንዲጸድቅ፣ ከ100,000 ብር በላይ ከሆነ ግን ለፕራይቬታይዜሽን ቦርድ ቀርቦ እንደሚፀድቅ ተደንግጎ ነበር። ሆኖም አነስተኛ የርክክብ ዋጋ ልዩነት ለቦርድ ቀርቦ እንዲፀድቅ ማድረግ የቦርዱን ጊዜ የሚሻማ በመሆኑ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ መመሪያው እንዲሻሻል ተደርጓል።

በዚሁ መሠረት በርክክብ ወቅት በመብለጥ ወይም በማነስ ለሚገኝ የርክክብ ልዩነት ዋጋ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 2 መሠረት ተተምኖ የገንዘቡ መጠን እስከ ብር 150,000 ከሆነ በዘርፉ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣ ከብር 150,001 እስከ ብር 250,000 ከሆነ በኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር፤ ከ250,000 ብር በላይ ከሆነ ደግሞ ለፕራይቬታይዜሽን ቦርድ ቀርቦ እንዲፀድቅ ይደረጋል።

ክ ፍ ል ስምንት

7. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

7.1 ስለ ዋጋ ተመን ማስተካከያ

የቋሚ ንብረቶች ወይም የንግድ ዋጋ በሚተመንበት ወቅት የመረጃ ወይም የሂሣብ ስሌት ስህተት መፈጸሙ ከተደረሰበት ድርጅቱ ለጨረታ ከመቅረቡ በፊት የዋጋ ማስተካከያ ይሠራለታል።

7.2 የመሸጫ ጠቋሚ ዋጋ ስለማጽደቅ

በዚህ መመሪያ መሠረት ለመጀመሪያ ጊዜም ሆነ ማስተካከያ ጥናት ተደርጕበት የተተመነ ድርጅት የጨረታ ጠቋሚ የትመና ዋጋ በፕራይቬታይዜሽን ቦርድ መጽደቅ አለበት፡፡ ሆኖም ለቦርድ ቀርቦ የዋጋ ትመና የፀደቀለት ድርጅት ዳግመኛ ጨረታ ማውጣት ሲያስፈልግ የዋጋ ትመናው ሦስት ዓመት ሞልቶት አዲስ የዋጋ ትመና ካልተሠራለት በስተቀር ዳግም ለቦርድ ማቅረብ አያስፈልግም፡፡

7.3 የዋጋ ትመና ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ

ሥራ ላይ ባለው የዋጋ ትመና መመሪያ መሠረት የድርጅቶች የዋጋ ትመና ፀንቶ የሚቆየው ለአንድ ዓመት ብቻ ሲሆን ልማት ድርጅቶቹ ዋጋ ትመና በተሠራላቸው ዓመት ውስጥ ካልተሸጡ በስተቀር በቀጣዩ ዓመት እንደገና የዋጋ ትመና መሥራት ስለሚጠይቅና ይህንን ሥራ በየዓመቱ ደጋግሞ መሥራት እሴት የማይጨምር ከመሆኑም በላይ የፕራይቬታይዜሽን ሂደቱን ሊገታ የሚችልበት ሁኔታ ስለሚፈጥር ይህንን ችግር ለመቅረፍ የትመናው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡

በዚሁ መሠረት የአንድ ድርጅት (አክሲዮን ማኅበር) የንብረት ዋጋ ወይም የንግድ ዋጋ ተመን ፀንቶ የሚቆየው የዋጋ ትመናው ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ ለሚቀጥሉት 3 ተከታታይ ዓመታት ይሆናል፡፡

7.4 ነባር መመሪያዎችና የአሠራር ልምዶች ተፈጻሚነት

ኤጀንሲው ከዚህ ቀደም ሲጠቀምባቸው የቆዩ የዋጋ ትመና መመሪያዎችና የአሠራር ልምዶች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

7.5 የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ከመጽደቁ በፊት ወደ ግል የማዛወር ሂደት ተጀምሮለት በመካሄድ ላይ ያለ የልማት ድርጅት ትመና በነባሩ የትመና መመሪያና አሠራር ተፈጻሚነቱ ይቀጥላል፡፡

7.6 መመሪያውን ስለማሻሻል

ማናቸውም በዚህ መመሪያ ላይ የሚደረግ ማሻሻያ በፕራይቬታይዜሽን ቦርድ ጸድቆ በሥራ ላይ እንዲውል ካልተፈቀደ በስተቀር ተፈጻሚነት የለውም።

7.7 መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከህዳር 1 ቀን 2005 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አባሪዎች:- ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አባሪዎች ለተሽከርካሪ ዋጋ ትመና የሚያስፈልጉ ሲሆን ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የመንግሥት ቋሚ ንብረት አስተዳደር ማኑዋል ላይ የተወሰዱ ናቸው::

አባሪ 1. የቋሚ ንብረቶች ዕድሜና የገበያ ዋጋ ተዛምዶ አወሳሰን ቀመር/ዘ/

ዕድሜ	ለሞተር ብስክሌት	ለትራክተር	ለአጭጾ መውቂያ	ለተሽከርካሪዎችና ሌሎች መሣሪያዎች
1	0.792	0.792	0.792	0.900
2	0.622	0.622	0.622	0.800
3	0.494	0.494	0.494	0.700
4	0.442	0.442	0.442	0.633
5	0.392	0.392	0.392	0.567
6	0.350	0.350	0.350	0.500
7	0.308	0.308	0.308	0.475
8	0.265	0.265	0.265	0.450
9	0.222	0.222	0.222	0.425
10	0.190	0.190	0.190	0.400
11	0.170	0.170	0.170	0.380
12	0.150	0.150	0.150	0.360
13			0.140	0.340
14			0.130	0.320
15			0.120	0.300
16				0.280
17				0.260
18				0.240
19				0.220
20				0.200
21				0.190
22				0.180
23				0.170
24				0.160
25ና ከዚያ በላይ				0.150